## ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል

## 39 ኛ ሳምንት

## ቤተክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት (III) - ልደተ ቤተክርስቲያን (III)

### የትምህርቱ ዓለማ

- ይህ ትምህርት ስለ ዘመነ ሐዋርያት የቤተክርስቲያን ታሪክ የምንማረው ተከታታይ ትምህርት አካል ነው።
- በዛሬው ትምህርታችንም ቤተክርስቲያን ስትወለድ የነበረውን የዓለም ሁኔታ እናያለን።

### የሚጠና ጥቅስ

- *"ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል……"* የሐዋ. ሥ. 17፣18

### የትምህርቱ ትኩረት

- ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ክርስቶስ በሥጋ በተገለጠበት ዘመን ስለ ነበረው የአይሁድ ሁኔታ ተምረናል።
- በዚህ ትምህርት ስለ አሕዛብ የሮም መንግሥት እንነጋገራለን።

### ለ.አሕዛብ

- እነዚህ ጣዖታትን የሚያመልኩ እና ስለእግዚአብሔር፣ስለኃጢአት ወይም ስለ ቅድስና አንዳች ትኩረት የሌላቸው የዓለም ክፍሎች ነበሩ።
- **የአሕዝብ ፍልስፍና** በክርስትና የመጀመሪያ ዘመን ከነበሩት ታዋቂ የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች አፊቆሮስና እስጢኢኮች ነበሩ።*"ከኤፊቆሮስ ወገንና ኢስጢኢኮችም ከተባሉት ፈላስፎች አንዳንዶች ከእርሱ ጋር ተገናኙ "* የሐዋ. 17፣18
- **የኤፊቆሮሶች** ፍልስፍና፡- ሁሉንም ሃይማኖቶች የሚቃወሙና በማንኛውም ሃይማኖት ያለ እምነት ኃጢአት ነው ብለው የሚያስቡ ናቸው።
- በሰማይ መለኮታዊ ኃይልና መሪ የለም ባዮች ሲሆኑ።አምላካቸው በአንድ በማይታወቅ ቦታ ራሱን አግልሎ የሚኖርና ስለ እነርሱም ሕይወት የማያስብ እንደሆነ ያምናሉ።ብዙ ሮማውያን በኢፊቆሮስ ፍልስፍና ያምናሉ።

**የእስጢኢኮች ፍልስፍና:**በአንድ እግዚአብሔር ያምናሉ፣ሁሉም ነገሮች ከአንድ መንፈስ ይወጣሉ እናም እያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር የሚወጣና የባሕርዩ ክፋይ የሆነ ጨረር ነው ይላሉ።

- ሰው ይህን ጨረር ሊጠብቀውና ለመልካም ነገሮችም ለያውለው ይችላል ብለው ያምናሉ።
- ከዚህም የተነሣ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የተሠጠው ልዩ ስጦታ አዕምሮ ነው፤ ብለው ያምናሉ።
- የአሕዛብ ጠባይ አሕዛብ የነበሩበትን የተመሳቃቀለ ኑሮ በጥሩ ሁኔታ የሚያስረዳን በሮሜ.1፣18-32 የተገለጠ ነው፡-*እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና ። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና ፤ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፣ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መሰለው ለወጡ።*
- *ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩስነት አሳልፎ ሰጣቸው ይህም የአውግዚአብሄርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፣ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው አሜን።*
- *ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ ወንዶችም በወንዶች ነው አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።*
- *እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሄርን የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይገባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ዓመፃ ሁሉ፣ ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት፣ ምላባቸው ቅትን፣ ነፍስ መግደልን ፣ ክርክርን፣ ተንኮልን፣ ክፉ ጠባይን ተሞሉ የሚያሾከሹኩ፣ ሐሜተኞች፣ አምላክን የሚጠሉ፣ የሚያንገላቱ፣ ትዕቢተተኞች፣ ትምክህተኞች፣ ክፋትን የሚፈላለጉ፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያስተውሉ፣ ውል የሚያፈርሱ፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ምሕረት ያጡ ናቸው። እንዚህ ለማያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሄርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።*

ሐ.የሮም መንግስት የአይሁድ ከተሞችና ሀገር ጠንካራና የተደራጃ በነበረው በሮማውያን ሥልጣን ሥር ነበር፡-
ሥፋቱ ፡- የአውሮፓ፣ የእስያ እና የተወሰነ የአፍሪካ ምድርንም ያጠቃልል ነበር።
የሮም መንግሥት አወቃቀር በተለያዩ ግዛቶች የተዋቀረ፣ለሁሉም ግዛቶች የዋናው የመገናኛ ከተማ ከሮም የተወከለ ሀገረ ገዥ ነበረው።እነዚህም ግዛቶች በሮም ሕግና የግብር ሥርዓት ይመሩ ነበር።

- ይህ የዚያን ዘመን ሕግ ሲሆን፣ በቅኝ ግዛት የተያገሮችና የተሸነፈ ሀገር ነዋሪዎች በቋሚነት ግብር እየገበሩ ይኖሩ ነበር።

- ለዚህም ነው ሮማውያን ሕዝቡን በቋሚነት የሚቆጥሩት" በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትዕዛዝ ወጣች ቄሬኔዎስ በሶርያ አገረ ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ጽሕፍት ሆነ። "ሉቃ. 2፣1

<u>የሮም ዜግነት ያላቸው ሰዎች መብቶች</u> በሮም ግዛት የሮም ዜግነት ያላቸው ልዩ ክብር ነበራቸው።

- "የሮም ዜግነት" መብቶች የሚሰጣቸው ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ነበር። ይህም በመግዛት፣በሮም ሠራዊት ውስጥ ወታደራዊ አገልግሎት በመስጠት ወይም በሮም ግዛት በመወለድ ነበር።
- የሚያገኙት ጥቅምም የሕግ ጥብቃ፣ ሳይከሰሱ አለመታሰር፣በሮም ከተማ የመዳኘት መብት ናቸው።" ***ስለዚህም ሊመረምሩት ያሰቡት ከእርሱ ወዲያው ተለዩ የሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ አሳስሮት ነበርና።"*** የሐዋ. ሥ. 22፣29 ***" ጳውሎስ ግን እኛ የሮሜ ሰዎች ስንሆን ያለ ፍርድ በሕዝብ ፊት ደብድበው በወኀኒ ጣሉን አሁንም በስውር ይጥሉናልን? አሁንም ራሳቸው ግን መጥተው ያውጡን አላቸው ።*** " የሐዋ. ሥ. 16፣37 ***" እንግዲህ በድዬ ወይም ሞት የሚገባውን ነገር አድርጌ እንደ ሆነ ከሞት ልዳን አልልም እነዚህ የሚከሱኝ ክስ ከንቱ እንደ ሆነ እነዚህ የሚከሱኝ አሳልፎም ወደ ቄሣር ይግባኝ ብዬአለሁ አለ።*** " የሐዋ. ሥ. 25፣17

<u>ከዚህ ምን እንማራለን?</u>

1) ክርስትና በመጀመሪያ ያገጠመው ፈተና ከሦስት ክፍሎች ነበር።ከአይሁድ፣ከአሕዛብና ከሮም መንግሥት ይህን ማወቅም መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ያግዘናል።
2) ክርስትና በጣም ጠንካራና የተደራጀ የተቃውሞ ኃይል አጋጥሞታል።ነገር ግን የእግዚአብሔር ኃይል ከዚህ ይልቅ ጠንካራ ነውና እነዚህን አሸንፎ በፍጥነት ተስፋፍቶል።
3) ክርስትና እነዚህን ኃይሎች ያሸነፈው በፀብና በዓመጽ አልነበረም።የሕዝቡን እምነትና የእግዚአብሔርን መንግሥት እየገነባ እንጂ። ስለዚህ ክፉን በመቃወም ጨለማን ከመርገም ሻማ ማብራት የሚባለውን አባባል ያስታውሰናል።
4) በዛሬው ማህበረሰብም በርካታ የተዛቡ ነገሮች አሉ።የክርስትናው መንገድም እነዚህን መርገም ሳይሆን በማረም መልካም አስተሳሰቦችን ማስፋፋት ነው።

ስንዴና እንክርዳድ

- የእናንተ ተግባር እንክርዳዱን መንቀል አይደለም፣ እንደ ስንዴው ማደግ እንጂ። የስንዴው አጫጅ ሲመጣ የስንዴያችሁን ጎተራ ምልቶ ስለሚያገኘው የእርሱ ጎተራ እስኪሞላ ድረስ ሠላሳ፣ ስድሳና መቶ ፍሬ ይሰበስባል።
- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሌሎች ሰዎችን ስሕተት በመቃወም ጊዜውን አላባከነም።
- እርሱ በዚህ ምድር ሳለ የሥጋዊ ዘመኑን ከሰዎች ስሕተትና ጥፋት እንዲሁም ከኅብረተሰቡና ከቤተ ክርስቲያን ጋር በመታገል አላሳለፈውም። የእርሱ ትኩረት የአዳዲስ መመሪያዎችን መሠረት መጣል፣ መገንባት፣ ሰዎች በእነዚህ መመሪያዎች እንዲያምኑና በሁሉም ሥፍራዎች እንዲያስፋፉ ማድረግ ነበር።
- እንክርዳዱን በመሰብሰብ ላይ ማተኮር ኃይል ማባከን ነው።
- ዲያብሎስ ባላችሁ ጊዜ ሁሉ በተለያዩ ችግሮች ባተሌ ሊያደርጋችሁና ማብቂያ የሌላቸው ስሕተቶችን ሊያቀርብላችሁ ዝግጁ ነው። የእርሱ ዋና ዓላማ እነዚህን ስሕተቶች በመዋጋት ራሳችሁንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ከመገንባት እንድትርቁ ማድረግ ነው።
- አንክርዳዱን በመንቀል ውስጥ ውሳጣዊ ሰላማችሁንና ከሰዎች ጋር ያላችሁን ሰላም ልታጡት ትችላላችሁ፤ በትግል ውስጥ መኖርን ጀምራችኋልና።
- ስለሆነም አርምሞአችሁን፣ የመንፈስ እርጋታችሁንና ትህትናችሁን ጨምራችሁ ታጡታላችሁ። እነዚህ ችግሮች ማብቂያ የሌለውን በሁከት የተሞላ ሁኔታና በማያቋርጥ ቁጣ እንድትከበቡ በሚያደርጓችሁ ልዩነቶች ውስጥ እንድትቆዩ ያነሳሷችኋል።
- ጨዋነታችሁንና ዝምታችሁን እንዳጣችሁት እንዲሁ ፈገግታችሁንም ታጡታላችሁ። ሰዎች ሁልጊዜ በአናንተ ላይ የሚመለከቱት ፈጋግታ የሌለበት ጭጋጋማ ገጽታን ነው። ንዴትና ኀዘን ስለሚቆጣጠሯችሁም ለእግዚአብሔር ስትሉ የደረሰባችሁ ንዴትና ኀዘን አድርጋችሁ ትቀበሉታላችሁ።
- ይህ ደግሞ ወደ ልብ ጭካኔ ልዩ ጭካኔ ይመራችኋል..........
- ሁልጊዜ የተሳሳቱት ላይ ትፈርዱባቸዋላችሁ፤ በስሕተቶቸው ላይ ታምጻላችሁ? ይህን በማድረጋችሁም በእነርሱ ዘንድ ያለውን እንክርዳድ እንደ መንቀል አድርጋችሁ ትወስዱታላችሁ። ሁልጊዜ ሰዎች ላይ ትጮሃላችሁ፣ ሰዎችን ትገሥጻላችሁ፤ ትቆጣላችሁ፣ በማንኛውም ነገርም ትበሳጫላችሁ።
- በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ለሰዎች ያላችሁን ፍቅርና ጨዋነታችሁን ታጡታላችሁ። በመሆኑም በሌሎች ሰዎች ዘንድ ያለውን እንክርዳድ ስትሰበስቡ በእናንተ ውስጥ ያለውን ስነዴ ትነቅሉታላችሁ። ከዚህ በኋላ ሰዎች በሁሉም ነገር ውስጥ የሚመለከቷችሁ እንክርዳድ አድርገው ነው።
- በተመሳሳይ ጊዜ ስንዴያቸውን ጠብቀው  እንክርዳዶቹን መንቀል የሚችሉት በጣም ጥቂቶች ናቸው። በመሆኑም እንክርዳዱን እንነቅላለን ሲሉ ስንዴውን እንዳይነቅሉ እግዚአብሔር ልቹን ይከለክላቸዋል።
- መጽሐፍ ቅዱስ ***"ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉ አትመልሱ..."*** (ሮሜ 12፡16) ብሎ በመናገሩ መልካም ብሏል።
- እንክርዳዶቹን ለመንቀል ወይም ለመሰብሰብ ተመራጩ መንገድ እነርሱን በመልካ ሥራ ማሸነፍ ነው። አንድ ጠቢብ ሰው "ጨለማውን ከማውገዝ ሻማ አብራ" በማለት ተናግሯል።

**ይቆየን።**